የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር አ1162/11/573

ቀን መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም.

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ለፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ወንጀል ምርመራ ቢሮ**

**አዲስ አበባ፣**

**ጉዳዩ፡- የኦሮሞ ነፃነት ንቅናቄ ፓርቲ ለቦርዱ ያቀረበውን ሀሰተኛ መረጃን በተመለከተ የወንጀል ምርመራ እንዲጀመር መጠየቅን ይመለከታል፤**

የኦሮሞ ነፃነት ንቅናቄ ፓርቲ መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው የኦሮሞ ባሕል ማዕከል የስብሰባ አዳራሽ ጠቅላላ ጉባኤውን አካሂዷል። በዚህ ጉባኤ ላይ በኢትዮጵያ የምርጫ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 79/2/ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤውን ለመታዘብ ከቦርዱ ሁለት ተወካዮች ተገኝተዋል። ጉባኤው ከመጀመሩ አስቀድሞ የጠቅላላ ጉባኤው የመድረክ መሪ 541 የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በስብሰባው ላይ እንደተገኙ ቆጣሪዎች ማረጋገጣቸውን በመግለፅ ስብሰባው እንዲጀመር አድርገዋል። ነገር ግን ጠቅላላ ጉባኤውን ለመታዘብ በስብሰባው ላይ የተገኙት የቦርዱ ተወካዮች ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት እና ስብሰባው እየተካሄደ እያለ በድጋሚ ለሁለት ጊዜያት ቆጠራ አካሂደው የተገኙት የጠቅላላ ጉባኤ አባላት 250 ብቻ መሆኑን አረጋግጠዋል። ይህንንም ጠቅላላ ጉባኤውን በመታዘብ መጋቢት 16 ቀን 2014 ዓ.ም. ለቦርዱ በቀረበ ሪፖርት ላይ ገልጸዋል።

ፓርቲው ሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ እንደመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 74/1/ሰ// እና በመመሪያ ቁጥር 3/2012 አንቀፅ 15 (ሁ) አስገዳጅ ድንጋጌ መሰረት የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ምልዓተ ጉባኤ የሚሟላው ቢያንስ 500 የጉባኤ አባላት ከተገኙ ነው። ከዚህ በተቃራኒ ፓርቲው ባካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፤



ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ስልክ +251 115 153468
ፋክስ +251 115 510025
ፌስቡክ /national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር @NEBEthiopia
ኢሜይል contact@nebe.org.et
ድረ-ገጽ www.nebe.org.et

1. ጠቅላላ ጉባኤው ሊጀመር ሲል **<u>541 የጉባኤ አባላት</u>** እንደተገኙ ተደርጎ በመድረክ መሪው መገለጹ፤

2. የቦርዱ ተወካዮች በጉባኤው መሃል ሁለት ጊዜ ቆጠራ ሲያከናውኑ **<u>የጉባኤው አባላት ብዛት 250</u>** ብቻ መሆናቸው መረጋገጡ፤

3. የጠቅላላ ጉባኤው አባላት ወደ ስብሰባ አዳራሹ ሲገቡ የተሳታፊዎች መመዝገቢያና መፈረሚያ ቅጽ ላይ ተመዝግበው ሲፈርሙ ስላልነበር ስለጉዳዩ የፓርቲው አመራር አባላት ተጠይቀው ተሳታፊዎች ወደ ስብሰባ ከመምጣታቸው በፊት መመዝገቢያ ቅጽ ተልኮላቸው ተመዝግበው እንደፈረሙ መገለጹ፤

4. ፓርቲው መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ኦነን/0113/2010 በተፃፈ ደብዳቤ መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 79/1 እና 3/ መሰረት በቦርዱ የተጠየቀውን መረጃ በትክክለኛ ሰነድ አስደግፎ የማቅረብ ግዴታ ተጥሎበት እያለ ፓርቲው በጠቅላላ ጉባኤው ላይ **<u>634 የጉባኤ አባላት</u>** ተገኝተዋል በሚል የስም ዝርዝርና ፊርማ የያዘ 41 ገጽ ሰነድ ለቦርዱ አቅርቧል።

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ፓርቲው ለቦርዱ ያቀረበው የስም ዝርዝርና ፊርማ በሃሰተኛነት የቀረበ ስለመሆኑ ምክንያታዊ ጥርጣሬ የሚያሳድር ሆኖ ተገኝቷል።

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀጽ 79/1/ እና 98/1ሠ/ መሰረት ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በአዋጁ የተዘረዘሩ መረጃዎችን እንዲያቀርብ በቦርዱ ሲጠየቅ በሰነድ የተረጋገጠ የጽሁፍ መረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ሲሆን በአንቀጽ 79/3/ እና 98/1ሠ/ ፓርቲው የሰጠው መረጃ ሃሰት መሆኑን እያወቀ ወይም የሀሰት መረጃ የሰጠ እንደሆነ ቦርዱ ተጠያቂ ሊያደርገው ይችላል።

በመሆኑም ፓርቲው የጠቅላላ ጉባኤ አባላትን ዝርዝር እና ፊርማ የያዘ በሚል ያቀረባቸው አጠራጣሪ ሰነዶች በወንጀል ምርመራ እንዲጣራ በማክበር ቦርዱ ያመለክታል።

ከበጎ ምኞት ጋር

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ

<u>አባሪ፣</u>

1. ፓርቲው መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም. ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ አስመልክቶ መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ኦነን/0113/2010 ለቦርዱ የፃፈው 01 ገጽ ደብዳቤ፤
2. ፓርቲው መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም. ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ አስመልክቶ የተያዘ 04 ገጽ ቃለ ጉባኤ፤
3. የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የያዘ 01 ገጽ ዝርዝር፤
4. የፓርቲው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ሆነው የተመረጡ ኃላፊዎች ስምምነት የገለፁበት 01 ገጽ ሰነድ፤
5. የፓርቲው የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ዝርዝር 01 ገጽ፤
6. የኦሮሞ ነፃነት ንቅናቄ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ (በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 መሠረት የተሻሻለ) 22 ገጽ፤
7. ፓርቲው መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም. ያካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ አባላት ዝርዝር 41 ገጽ።
8. በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤው ላይ የተገኙት ሁለት የቦርዱ ታዛቢዎች በመጋቢት 16 ቀን 2014 ዓ.ም የጠጉባኤውን ሂደት በተመለከተ ለቦርዱ ያቀረቡት 04 ገጽ ሪፖርት።